## ለሁሉምሚዲያ አካላት

## <u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ ፡ - የኮሮና ቫይረስ በሽታ(የኮቪድ-19) አስሜልክቶ የተዘጋጀ ጋዜጣዊ መግለጫ**

**የካቲት 24/2012**

### በዓለምአቀፍ ደረጃ የኮሮና ቫይረስ በሽታ(ኮቪድ -19) ስርጭት

- በዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርት ማሰረት እስከ የካቲት 24 /2012 ይህ ሚጃ እስከ ተጠናከረበት ጊዜ ድረስ በዓለምአቀፍ ደረጃ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰባት (89,527) ሲሆን ሶስት ሺህ ሃምሳ ስድስት (3,056) ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸውአልፏል፡ ፡
- በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ያሏቸው መሆኑን አዲስ ሪፖረት ያደረጉትን አዘርባይጃን፣ ኢኳዶር፣ አየርላንድ፣ ሞናኮ፣ ኳታር ፣ ሜክሲኮ፣ ሳንሜሪኖ፣ አርሜኒያ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ዶሚኒካ ሪፐብሊክ፣ ሊክሰምበርግ፣ አይስላንድ፣ ኢንዶኔዥያ እና ቤላሩስ ጨምሮ በስድሳ ሰባት (67) ሀገራት ውስጥሪፖርት ተደርጓል::

### በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በመካሄድ ላይ ያለ የዝግጅት ሁኔታ

#### ከባለፈውጋዜጣዊ መግለጫማለትምከየካቲት 20/2012 ጀምሮ ይህ ሚጃ እስከ ተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ያሉ አዲስ ሚጃዎች

- በሁሉም ወደ ሀገር መግቢያ ጣቢያዎች አርባ ሺህ አምስት መቶ አስራ ስምንት(40,518) በሙቀት ማለያ (ኢቦላና ኮቪድ-19 በማጣመር) አልፈዋል፡ ፡
- በቦሌ አውሮፕላን ሚረፊያ በ7ቱ መግቢያዎች ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ (21,750) በላይ የሚሆኑ መንገደኞች በሙቀት ልየታው ያለፉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አምስት መቶ ስምንት (508) በሽታውን ሪፖርት ካደረጉ ሃገራት የማጡናቸው ፡
- በሽታውን ሪፖርት ከተደረገባቸውአገራት የማጡተጓዞች የጤና ሚጃ ቅጽ ከሙሏታቸው በተጨሜሪ ባሉበት ቦታ ለ14 ቀናት በስልክ የሚደረግ የጤና ክትትል ክትትል ተደርጎላቸው ያጠናቀቁ ሰባት መቶ ሃምሳ ስድስት (756) ሰዎች ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሁለት (932) የሚሆኑት ደግሞየጤና ክትትል ላይ ይገኛሉ፡ ፡
- ሰባት (7) አዳዲስ ጭምጭምታዎች ለኢንስቲትዩቱ የድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል (Public Health Emergency Operation Center) የደረሱ ሲሆን በሁሉም ጥቆማዎች ላይ ማጣራት ስራ ተደርጎ ሶስት (3) ታካሚዎች የበሽታው ተማሳሳይ ምልክት በማሳየታቸው በለይቶ ማቆያ ክትትል እየተደረገላቸው የነበረ ሲሆን የላቦራቶሪ ምርሚራ ተደርጎላቸውከቫይረሱ ነጻ መሆናኑቸውተረጋግጦ ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡ ፡

- በአጠቃላይ ከጥር 15 ጀምሮ እስካሁን ድረስ ዘጠና (90) ጫምጫምታዎች ለኢንስቲትዩቱ የድንገተኛ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል ደርሰውበሁሉም ጥቆማዎች ላይ ማጣራት ስራ ተደርጓል፡፡ ከነ ዚህም ውስጥ ሃያ አራቱ (24) የበሽታው ተማሳሳይ ምልክቶች በማሳየታቸውእና በሽታውን ሪፖርት ያደረጉ አገራት የጉዞ ታሪክ የነበራቸው ስለሆነ በተለያየ ጊዜ በለይቶ ማቆያ ማእከል እንዲቆዩ ተደርጓ የላብራቶሪ ምርመራ ውጤታቸውከቫይረሱ ነጻ መሆናቸውበመረጋገጡወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ሰአት ምንም አይነት ተጠርጣሪ በለይቶ ማቆያ ውስጥየሌለ መሆኑን ኢኒስቲትዩቱ ያሳውቃል፡፡

## በመካሄድ ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት

- የኮሮና ቫይረስ በሽታ ለመከላከል ክትትል የሚያደርግ ብሔራዊ ሚኒስትሮች ግብረሃይል ተቋቁሟል፡፡ ኮሚቴው ስድስት አባላት ያሉት ሲሆን እነሱም የሠላም ሚኒስትር የሆኑት ክብርት ወ/ሮ ሚሪያት ከሚል፤ የገንዘብ ሚኒስትር የሆኑት ክቡር አቶ አህመድ ሺዴ፤ የገቢዎች ሚኒስትር የሆኑት ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፤ የትራንስፖርት ሚኒስትር የሆኑት ክብርት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ እና የጤና ሚኒስትር ደኤታ የሆኑት ክብርት ዶ/ር ሊያ ታደሠ ናቸው፡
- ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ሰራተኞች፤ ከሁሉምክልል ለማጡላብራቶሪ እና ጤና ባለሞያዎች የግንዛቡ ማስጨበጫስልጠናዎች እና የማበቃት ስራዎች በፌደራል እና በክልሎች ተጠናክሮ እየቀጠለ ነው፡
- በምድር ኬላዎች ላይ እና በዓለምዓቀፍ አየር መንገዶች የሚደረጉ የልየታ ስራዎች እንደቀጠሉ ናቸው፡
- ከዓለም የጤና ድርጅት እራስን ከበሽታ ለመከላከል የሚያገለግሉ ግብአቶች እና ለልየታ ስራ የሚውሉ የሰውነት ሙቀት መለኪያ መሳሪያዎችን ማገሱ ይታወቃል፡፡ እነዚህንም ግብአቶች ለክልሎች፣ ለሆስፒታሎች እና ለልየታ ቦታዎች እየተሰራጩ ይገኛሉ፡፡
- የአደጋ ጊዜ ቅድመዝግጅት እና ምላሽ እቅድ ተዘጋጅቶ ለማግስት እና ለባለድርሻ አካላት ገቢ ተድርጓል፡፡ በዚህም ማሰረት የገቢ ማሰባሰብ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የኮሮና ቫይረስ በሽታ የመከላከል እና ክትትል የሚያደርግ ግብረሀይል በቅርበት በመገናኘት ቫይረሱን በመከላከሉ ዙርያ ያሉ ስራዎች ላይ የሚያደርጓቸውን ውይቶች እንደቀጠሉ ይገኛሉ፡፡
- ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ማኔጅመንት ቦርድ አባላት እና ዋና ስራ አስኪያጅ ጋር ስለ ኮቪድ-19 በሽታ የመከላከያ መንገዶች ውይይት ተድርጓል፡፡
- ከቻይና በተጨማሪ ከኮሪያ ፤ጃፓን ፤ከኢራን ኢስላሚ ሪፐብሊክ እና ጣሊያን የሚመጡተጓዞችን የልየታእና የህክምና ቅጽ በማስሞላት ክትትል ማድረግ ቀጥሏል
- በተለያዩ የክልል ከተሞች ፣ የአየር መንገዶች እና የድንበር ኬላዎች የሚገኙ የልየታ እና የማቆያ ቦታዎች የቫይረሱን መከላከያ የሚሆኑ ግብአቶች ለማሟላት የሚሰሩ ስራዎች በማሰራት ላይ ይገኛሉ
- የጤና ሚኒስተር ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ቫይረሱን ከመከላከል አንጻር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየሰራ ይገኛል፡፡

- የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ለሚኙ ስድስት መቶ ሃምሳ አምስት (655) የጤና ባለሞያዎች በአምስት ዙር ስለኮሮና ቫይረስ በሽታ ስልጠና ማስጠት ተጀምሯል፡፡
- የጤና አጋር እና ለጋሽ ድርጅቶች የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚኙውየድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል መገብኘታቸውየሚታወስ ሲሆን ከኢኒስቲትዩቱ ጋር የኮቪድ -19 በሽታን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ ስራዎችን አስሚልክቶ እየተወያዩ ይገኛል፡፡

የኮሮና ቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) የዓለምስጋት የሚሆኑ ማጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በሜጨምር ላይ ይገኛል፡፡ እስካሁን ባለውሚረጃ በሽታውየተያዙ ሰዎች 80 በመቶ ቀለል ያለ የመተንፈሻ አካል ህመም፤ 14 በመቶ በከባድ እና 5 በመቶ የሚሆኑት ሰዎች በጽኑ እንደሚታመሙያማላክታል፡፡ ህመሙእድሚያቸውበገፉ የማህበረሰቡ አባላት እንዲሁም የረጅምጊዜ ታካሚዎች ማለትምየስኳር፤ የግፊት፤ የልብ፤ የኤች. አይ.ቪ/ ኤድስ እና የካንሰር በሽታ ታካሚዎች ለከፋ የጤና እክል ያጋልጣል፡፡ በሽታውከመተንፈሻ አካል በተጨማሪ የልብ እና የኩላሊት ስራ ማቆም በማስከተል ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው፡ ስለበሽታውከትክክለኛ ምንጭች ማለትምከዓለምየጤና ድርጅት፤ ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ሚኒስተር እንዲሁምየኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት ሚረጃ በመውሰድ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እናሳስባለን፡፡

ህብረተሰቡ ከዚህ በፊት ማንኛውምበሽታ ለመከላከል ሲጠቀምባቸውየነበረውን የበሽታ መከላከያ መንገዶች ችላ ሳይል አጠናክሮእንዲቀጥል እንመክራለን፡፡

ማለትም

- የእጅ ንጽህና በውሃ እና ሳሙና አዘውትሮ ሙታጠብ
- ለእጅ ንጽህና ማጠበቂያ የሚሰሩ አልኮል ነክ ምርቶችን አዘውትሮ ማጠቀም
- ባልታጠበ እጅ አይን፤ አፍንጫእና አፍን አለመንካት
- ቫይረሱን ሪፖርት ከተደረገባቸውአገሮች የማጡተጓዦች ሆነ ውየበሽታውን ምልክት ከሚያሰዩ ሰዎች ጋር ንክኪ አለማድረግ በተጨማሪ ምከ 1-2 ሜትር ርቀት ማጠበቅ
- ስለበሽታውበቂ ሚረጃ በማግኘት መተግበር ይገኙበታል፡፡

የኮቪድ-19 በሽታ አሳሳቢ ደረጃ በደረሰበት በዚህ ጊዜ በተለየምሜኛውምህመምያለባችሁ ተጓዦች በሽታው ወደ አደረጉ አገራት የምታደርጓቸውን ጉዞዎች እንድታዘገዩ ቢቻል እንድታቋርጡይመከራል፡፡ ማንኛውምተጓዦች በምትሄዱበት ሀገራት ሁሉ ተገቢውን ጥንቃቄ እንድታደርጉ እናሳስባለን፡፡

የኮሮና ቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) ካለባቸውአገሮች የማጡከሆነ

- በአገራችን መግቢያ እና መውጫበታዎች የሚደረገውን የልየታ አገልግሎት ማግኘትዎን ያረጋግጡ
- ስለነበርዎት ጉዞ የተሟላ እና ትክክለኛ ሚረጃ እንዲሁምበሀገር ውስጥ ስለሚጠቀሙት አድራሻ ማስጠቶን አይዘንጉ
- እራስዎን ከሌሎች ሰዎች እና ከቤተሰብ አባላት ለ14 ቀናት በማገለል ጤናዎን ይከታተሉ!
- በየዕለቱ የጤናዎትን ሁኔታ ለመከታተል ለሚደውሉ ባለሞያዎች ትክክለኛ ሚረጃ በማስጠት ይተባበሩ!

- ትኩሳት፣ ሳልና የመተንፈስ ችግር ካጋጠሞት ለስቸኳይ የህክምና እርዳታ 8335 ይደውሉ፤
- በሚያስሉበት እና በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፍና አፍንጫዎትን ክንድዎን በማጠፍ ወይም በሶፍት ይሸፍኑ፤ እጅዎን በሳሙና በውሃ ይታጠቡ!

**ትኩረት ሚደረግ ያለባቸውጉዳዮች**

- የኮሮና ቫይረስ በሽታ ነጭ ጥቁር የቆዳ ቀለም ሳይለይ ሁሉንም የሰው ዘር የሚያጠቃ በሽታ ነው፡
- አስካሁን የተረጋገጠ መድሐኒት ወይም ክትባት የሌለው በመሆኑ ሕብረተሰቡ ይህንን በሚዳት እና የጥንቃቄ መንገዶችን በማወቅ እንዲሁም በመተግበር በሽታውን ማካላከል ይኖርበታል፡፡
- በተጨማሪ ምህብረተሰቡ በሀገራችን እስከ አሁን በቫይረሱ ማያዙ የተረጋገጠ ሰው አለመኖሩን አውቆ ሳይዘናጋ የበለጠ ጥንቃቄ ኢንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ ያሳስባል፡፡

ለተጨማሪ ሚረጃ በነፃ የስልክ ማስመር 8335 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 ወይምበኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በማጠቀምማግኘት ይቻላል፡፡

---

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

የካቲት 24/2012